# የከተሞች ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮግራም የከተሞችን ጽዳትና ውበት ለመጠበቅ የሚኖረው ጠቀሜታ

አብርሃም ጴጥሮስ
በከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር
የፌዴራል የከተሞች ስራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲ

መጋቢት 2009
አዲስ አባባ፣ ሂልተን ሆቴል

ሀገር አቀፍ የከተማ ጤና ጉባኤ
NATIONAL CONFERENCE ON URBAN HEALTH
APRIL 3-4, 2017, HILTON HOTEL, ADDIS ABABA, ETHIOPIA

# የፕሮጀክቱ ዓላማና ሽፋን

የኢትዮጵያ መንግስት በከተሞች እየታየ ያለውን የምግብ ዋስትና እጦት ተጋላጭነት ለመቀነስ የሚያስችል የከተሞች የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ ቀርጾ ሚያዝያ 30/2007 ዓ.ም የሚንስትሮች ምክር ቤት ባካሄደው 84ኛ መደበኛ ጉባኤ ጸድቋል፡፡

- በስትራቴጂው መነሻነት በከተሞች ከድህነት ወለል በታች የሚገኙትን ዜጎች የምግብ ዋስትና እጦት ተጋላጭነትን መቀነስ ዓላማ ያደረገ የአስር ዓመት ፕሮግራም ተቀርጿል፡፡
- ግቡ በ972 ከተሞች የሚገኙ ከ4.7 ሚ በላይ ዜጎች የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ ነው፡፡
- ለጊዜው ፕሮጀክቱ ተግባራዊ የሚሆንባቸዉን 11 ከተሞች (መቀሌ፣ አዲስ አበባ፣ አዳማ፣ ሀዋሳ፣ ደሴ፣ ድረዳዋ፣ ሀረር፣ ጅግጅጋ፣ ሰመራ ሎጊያ፣ ጋምበላ እና አሶሳ) ናቸው፡፡
- እስከ **604,000** ተጠቃሚዎችን በሂደት መለየትና ተጠቃሚ ማድረግ፣(ከሀገሪቱ 12 ከተመረጡት ከተሞች ደግሞ 55 %ያህሉን የሚሸፍን ነው፡፡

# የቀጠለ...

- የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሴፍቲኔት ድጋፍ ከማቅረብ ጎን ለጎን የዘላቂ ኑሮ ማሻሻያ ድጋፍ መስጠትና ተጠቃሚዎች አሁን ከሚገኙበት የኑሮ ሁኔታ የሚላቀቁበትን የረጅም ጊዜ ዓላማ የያዘ ነው፣
- የአገልግሎት አቅርቦቱ የመሥራት አቅም ላላቸዉ በሚያደርጉት የጉልበት አስተዋጽዖ ልክ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግና አቅም ለሌላቸዉ በቀጥታ ድጋፍ ንዑስ ፕሮግራም ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ነው፣
- የገንዘብ ድጋፉ ጊዜያዊ የምግብ ችግርን ለማቃለል ሲሆን፤ የኑሮ ማሻሻያ ድጋፉ ግን የቤተሰብ ገቢን በዘላቂነት ለማስፋትና ለማሻሻል የሚያግዝ ነዉ፣

# የፕሮጀክቱ ዋና ዋና ምሰሶዎች

1. **የሴፍቲ ኔት ድጋፍ፡** በአካባቢ የልማት ሥራና ቀጥታ ድጋፍ ተጠቃሚዎች የገንዘብ ድጋፍ ማቅረብ
2. **የዘላቂ ኑሮ ማሻሻያ ፡** ሥራን ማበረታት (የግል ሥራን ፣ የቅጥር ሥራን ማበረታትና የክህሎት ሥልጠና ድጋፍ ማድረግ)
3. **ተ ቋማት የማጠናከርና የፕሮግራም አመራር ድጋፍ፡-**
   1. የተጠቃሚዎች ልየታ (minimizing inclusion & exclusion error)
   2. ክትትልና ግምገማ እና የማኔጅመንት ኢንፎርሜሽን ሥርዓት መዘርጋት
   3. ዘመናዊ የክፍያ ሥርዓት መዘርጋት
   4. የህብረሰብ እና የባለድርሻ አካላት ተሳትፎን ማጠናከር
   5. የአቅም ግንባታ ስራዎች በየደረጃው መስራት
   6. የፕሮግራም አመራር (የፋይናንስ ስራ አመራር እና የግዢ ስራ አመራር) ስርዓት መዘርጋት

# የሴፍቲ ኔት ድጋፍ አይነቶችና የከተማ ፅÎዳትንና ውበትን ለመጠበቅ የሚኖራቸው ሚና

- የሴፍቲኔት ድጋፍ በሁለት ይከፈላል፣
- <u>**አንደኛው**</u> ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በዕድሜ፣በተደራራቢ አካል ጉዳት እና በኤችአይቪና ሌሎች በሽታዎች ምክንያት መስራት ለማይችሉ ዜጎች በየወሩ የሚሰጥ የገንዘብ ድጋፍ ነው፡፡በዚህ ድጋፍ በአንድ ቤተሰብ እስከ አራት ሰው ተጠቃሚ ሊሆን ይችላል፡፡የክፍያውም መጠን ወደፊት በጥናት የሚሻሻል ሆኖ 170 ብር ይሆናል፡፡
- <u>**ሁለተኛው**</u> የሴፍቲኔት ድጋፍ በቅድመ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ማንኛም መስራት የሚችል ዜጋ በአካባቢ ልማት ስራዎች ተሰማርቶ በሚያገኘው የጉልበት ዋጋ ራሱ እና ቤተሰቡ ከምግብ ዋስትና እጦት ተጋላጭነት ይታጋል፡፡
- ይህ የድጋፍ ዓይነት የዜጎችን የምግብ ዋስትና ችግር ከመፍታት ባሻገር ከተሞችን ፅዱና አረንጓጌ በማድረግ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡

# የአካባቢ ልማት ስራዎች ጠቀሜታ ፣

- ለተጠቃሚዎች በዓመት 12 ወራት በአጠቃላይ የ3 ዓመት ድጋፍ ማድረግ
  - በአማካይ 4 አባላት ላለዉ ቤተሰብ በዓመት የሚሳተፉበት የስራ ቀናት፡-
    1. ለመጀመሪያዉ ዓመት 240 ቀናት፣
    2. ለሁለተኛ ዓመት 160 ቀናት፣
    3. ለሦስተኛ ዓመት 80 ቀናት፣
- በከተሞች ልማታዊ ሴፍቲኔት የሚሰሩ የአካባቢ ልማት ስራዎች የዜጎችን የምግብ ዋስትና ከማረጋገጥ ባሻገር ከተሞቻችንን ፅዱና አረንጓዴ በማድረግ ለአየር ንብረት ለውጥ አይበገሬ ከተሞችን የመፍጠር ትልቅ ዓላማም ጭምር ያለው ነው፡፡
- ከዚህም በተጨማሪም ስራዎቹ ለኑሮ ምቹ ያልሆኑ የሴፍቲኔት ተጠቃሚ ሰፈሮችን የማልማትና የደቀቁ ቦታዎችን በማስተካከል ለከተማ ግብርና ምቹ ማድረግን ያለመ ነው፡፡
- የተመረጡ የአካባቢ ልማት ስራዎች፤የደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ፣የአረንጓዴ ልማት፣የተቀናጀ የተፋሰስ ልማት፣የሴፍቲኔት ተጠቃሚ ሰፈሮች መሰረተ ልማት እና የተጎዱ ሰፈሮችን በማልማት ለከተማ ግብርና ምቹ ሁኔታ መፍጠር ናቸው፡፡

# ጉልበትን የሚጠቀሙ የአካባቢ ልማት ሥራዎች፣

በህብረተሰቡ ፍላጎት ላይ በመመሥረት የሚሠሩ የአካባቢ ልማት ስራዎች በአምስት ስራዎች ላይ ብቻ የተወሰነ ይሆናል፡-

1. ደረቅ ቆሻሻ አያያዝና አወጋገድ፤ይህንን ስራ በስታንዳርድ መስራት የሚያስችል ማንዋልና አስር ፓኬጆች ተዘጋጅተዋል፡፡(የገበያ ቦታዎች ጽዳት፣የቀልዝ ዝግጅት፣የመንገድ ፅዳት፣የወረቀትና ፕላስቲክ ቆሻሻን መልሶ መጠቀም፣......)
2. የከተሞች  አረንጓዴ ልማት ስራ፣(የስፖርት ማዘውተሪያ አረንጓዴ ልማት፣የመዝናኛ ፓርኮች ልማት፣የመንገድ አካፋይ፣አደባባይናዳርቻ ልማት፣ፕላዛና ክበረ በዓል ቦታዎች፣የሰፈር ውስጥ ክፍት ቦታዎች፣የዘላቂ ማረፊያ...)
3. የተቀናጀ ተፋሰስ ስራ፤ ይህ ስራ በከተሞች የሚታየውን የውሃ ችግርና የጎርፍ አደጋን ይፈታል፣ የወንዝ ዳርቻ፣የስነ አካላዊ አፈርና ውሃ ጥበቃ ፓኬጆች ተዘጋጅቷል፡፡
4. የከተማ መሰረተ ልማት ግንባታ ስራ( የሚሰራው በተመረጠው ቀጠና ብቻ ነው)፣
5. የከተማ ግብርና ሥራዎችን ለማከናወን የሚያስችሉ ቦታዎች ማዘጋጀት፣

# የህብረተሰብ ተሳትፎ፣

የህብረተሰብ ተሳትፎ ዓላማዉ ህብረተሰቡ ስለ ፕሮጀክቱ ግንዛቤ ኖሮትና መብቱንና ሃላፊነቱን ተረድቶ በዕቅዱም ሆነ በአፈፃፀሙ አግባብ ያለዉን ተሳትፎ እንዲያደርግ ነዉ፣

ሦስቱ ዋና ዋና ተግባራት

- በፕሮጀክቱ ገንዘብ አጠቃቀም ሥርዓት ግልጽነትና ተጠያቂነት ለማስፈን ስለ ፋይናንስና በጀት መረጃና ዕዉቀት እንዲያገኙ ማድረግ፣
- በፕሮጀክቱ ተጠቃሚዎች እና በአካባቢ ልማት ስራዎቸ  መረጣ ላይ እንዲሳተፉና የሚነሱ ልዩ ልዩ ቅሬታዎችን በአግባቡ ለማስተናገድ እንዲቻል የግንዛቤ ሥራ በህብረሰቡ ዘንድ መሥራት፣
- በሥልጠናና በልዩ ልዩ ዘዴ  ህብረተሰቡ በፕሮጀክቱ ዕቅድ ዝግጅት፣ ቅድሚያ በሚሰጡ ተግባራት ላይ እና የፕሮጀክት አፈፃፀም ላይ ጉልህ ተሳትፎ እንዲኖራቸዉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡



# የተጠቃሚዎች ልየታ

- በመልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ
- በሰፈር እና ቀጠና ኮሚቴዎች
- እራስን በተቀመጠው መስፈርት መሰረት ለፕሮግራሙ እጩ በማድረግ
- የኑሮ ደረጃ ምዘና
- የአራቱ ጥምር ምዘና



# የከተሞች ምግብ ዋስትና ፕሮግራም ቅድመ ዝግጅት ስራዎች አፈጻጸም

## በፌዴራል ደረጃ

- የፌዴራል የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራና ምግብ ዋስትና ኤጀንሲን መልሶ የማደራጀት ተግባር ተከናውኗል፣
- የፕሮጅክት ማስተባበሪያ ዩኒት ተደራጅቷል፣
- የተለያዩ ማስተግበሪያ መመሪያዎች፣ ማንዋሎች ዝግጅት ተገባዷል፣ ( የፕሮጅክት ማስተግበሪያ ፣ የግዥ፣ የፋይናንስ፣ ለአካባቢ ልማትና ለዘላቂ ኑሮ ማሻሻያ ፕሮግራሞች ማስፈጸሚያ ፓኬጆች ፣ ጋይድ ላይኖችና ስታንዳርዶች፣ የመመልመያ መመሪያ፣ የቅሬታና የማበረታቻ መመሪያ ) ተዘጋጅተዋል፡፡

# የቀጠለ

- በፌደራል ደረጃ  ፕሮግራሙን በበላይነት የሚመራ እና የሚደግፍ 22 ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች አባል የሆኑበት ምክር ቤት ተቋቁሞ ስራ ጀምሯል፤
- የአካባቢ ልማት ቴክኒክ ኮሚቴ፣የቀጥታ ድጋፍ ቴክኒክ ኮሚቴ፣የዘላቂ ኑሮ ማሻሻያ ቴክኒክ ኮሚቴ  ተቋቁሞ ስራ ጀምሯል፤
- እነዚህን ቴክኒክ ኮሚቴዎች የሚያስተባብር የማኔጅመንት ኮኦርዲኔሽን ኮሚቴም ስራውን ጀምሯል፤በክልሎችና በከተሞችም ተመሳሳይ አደረጃጀት ተሰርቷል፡፡

# አመሰግናለሁ

